# አንድነት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር

**ANDINET NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT ORGANIZATIONS (ANAASO)**

1334 9th Street, NW. Suite # 1 Washington DC. 20001.
Tel: (202) 462 0556 Fax: (202) 462 0557 Email: info@andinetusa.org


## <u>የነጻነት ታጋዮችን መግደል ትግሉን ያጠናክረዋል እንጂ አያዳክመውም</u>

በሀገራችን በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ሥርዓት እንዲዘረጋና ሕዝቡ የመብቱና ያገሩ ባለቤት እንዲሆን የሚደረገዉ ትግል ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ይገኛል። ለአሥራ ስምንት አመታት በሕዝቡ ላይ የግፍ ቀንበር የጫነዉ ገዢዉ ፓርቲ አሁንም እንደለመደዉ በኃይልና በጠመንጃ ሕዝቡን እየረገጠ ለመግዛት እኩይ ተግባሩን እየፈጸመ ነዉ።

በፊታችን ግንቦት በሚደረገዉ ምርጫ፣ ለሕዝቡ ብቸኛ አማራጭ የሆነው አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ አባልና ምሰሶ የሆነበት መድረክ፣ በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅ፣ በምዕራብና በመሃል የአገራችን ግዛቶች በሙሉ ሥር የሰደደና ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። ተቃዋሚዎችን በማፈንና በማንገላታት፣ ሕዝባዊ ስብሰባዎች እንዳያደርጉ መሰናክል በመፍጠር፣ የሕዝብ የመገናኛ ሚዲያዎችን ሙሉ ለሙሉ በመቆጣጠር፣ ከምዕራባዉያን በእርዳታ በሚገኘዉ ገንዘብ አባላትን በመግዛትና እንደ አፓርታይድ ሥርዓት የኢሕአዴግ አባላት ብቻ የሥራና የስኮላርሺፕ እድል እንዲያገኙ በማድረግ ስልጣኑን ለማራዘም ከዘጠና ሰባቱ ምርጫ ዉርደት ጀምሮ ሲሰራበት ቆይቷል።

አፈራረስኩት ያለዉ የቅንጅት መንፈስ በአንድነት ስምና በወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ መሪነት እንደገና መታየት ሲጀምር፣ ጭፍናዊ በሆነና ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ እኝህን ታላቅ የሕዝብ መሪ ወደ ቃሊቲ እሥር ቤት ወረወረ። የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር ግን ትግሉን አላዳፈነዉም። ይበልጥ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ አርዓያ ሆነዉ በርካታ ታጋዮችን ወለዱ።

ወ/ት ብርቱካን ከቃሊቲ ሆነዉ በሚመሩት በዚህ ሠላማዊ ትግል፣ ሰሞኑን በምርጫ ሂደት እያየነዉ እንዳለ፣ ከባድ መስዋእትነት እየተከፈለ ነዉ። መድረኩን ወክለዉ በአድዋ አካባቢ ለመወዳደር ተመዝግበዉ የነበሩ ጠንካራ የዴሞክራሲ ታጋይ፣ አቶ አረጋዊ ገብረዮሐንስ፣ ኢሰብአዊና አረመኔያዊ በሆነ መንገድ በወያኔ/ኢሕአዴግ ታጣቂዎች ተገድለዋል።

እኝህ ጀግና በወጣትነት እድሜያቸዉ «አገሬን እረዳለሁ፣ ሕዝቤን አገለግላለሁ» ብለዉ የተነሱ ኢትዮጵያዊ ነበሩ። ነገር ግን ኢትዮጵያዉያን ባርያ ሆነዉ፣ ድሃ ሆነዉ፣ ተረግጠዉ፣ ሕሊናቸዉን ሸጠዉ እንዲኖሩ እንጂ ቀና እንዲሉ፣ ለመብታቸዉ እንዲቆሙ፣ ከራሳቸዉ አልፈዉ ለሌሎች እንዲተርፉ የማይፈልገዉ ወያኔ/ኢሕአዴግ፣ ብርቱካን ሚደቅሳ እሥር ቤት በከተተበት ክፉ መንፈሱ፣ የአቶ አረጋዊን ደም በምድረ ትግራይ እንዲፈስ አድርጓል።

ሌላዉ መድረኩን ወክለዉ በአክሱም አካባቢ ዉቁሮ ከተማ ለፓርላማ የሚወዳደሩ አቶ አያሌዉ አየለ የሚባሉ ታጋይም እንደዚሁ፣ አሁንም በኢሕአዴግ ታጣቂዎች ተደብድበዉ በሞትና በሕይወት መካከል ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ አገራችን፣ ሰዉ በጎ ባደረገ፣ ለፍትህ በቆመ፣ ለሕዝብ መብት በታገለ፣ ሕግን እናስከብራለን በሚሉ ተደብድቦ የሚገደልበት አገር መሆኗ በጣም የሚያሳዝንና ዉስጥን የሚያደማ ሁኔታ ነዉ።

አቶ አረጋዊ በዚህ በወጣትነት እድሚያቸዉ ከዚህ አለም በሞት መለየታቸዉ እጅጉን የሚያሳዝንና የሚያስለቅስ ነዉ። ሁላችንም የተሰማንን ከፍተኛ ሃዘን እየገለጽን፣ ለአቶ አረጋዊ ቤተሰቦች፣ ዘመድና ወዳጆች በሙሉ እግዚአብሄር ያጥናቹህ፣ የአቶ አረጋዊን ነፍስ እግዚአብሄር ይማር እንላለን።

ወያኔ/ኢሕአዴግ በትግራይ የመድረኩ ተወዳዳሪዎች ላይ ያደረሰዉ ግፍ የሚያሳየዉ ድርጅቱ በዉስጡ ቀፎ እንደሆነ፣ እንደፈራ፣ በራሱ እንደማይተማመን፣ እድሜዉ አጭር እንደሆነ ነዉ።

ዜጎች እየታሰሩ፣ ወገኖቻችን ደማቸዉን እያፈሰሱ፣ ከሥራ እየተባረሩ፣ ከፍተኛ እንግልት እየደረሰባቸዉ ይህን አምባገነን ዘረኛ አገዛዝ እየታገሉት ነዉ። እኛም ከመቼዉም በላይ ለትግሉ እንድናነሳሳ፣ ከዝምታችን እንድንወጣ፣ የለበስነዉን የተሰፋ መቁረጥና የሽንፈት ካባ እንድናወልቅና የመሠረት ድንጋይ የሆነዉን በአገር ቤት የሚደረገዉን ትግል ለመደገፍ እንድንሰባሰብ ያስፈልጋል። በትግራይ የፈሰሰዉ የአቶ አረጋዊ ደም ደዉል ሆኖ በአይምሮዋችን ሊያቃጭልብን ያስፈልጋል።

ወገኖቻችን እየሞቱ፣ እየታሰሩ፣ እየተንገላቱ በተከፈተዉ ትንሺ ቀዳዳ እልህ አስጨራሽ ትግል እያደረጉ ባለበት ሁኔታ፣ የተለያዩ ምክንያቶች እየሰጠን ወደ ኋላ ማለት ታሪካዊ ስህተት መሆኑን እናስገነዝባለን። የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ እንዲሁም የመድረኩ አባላትና ደጋፊዎች በአገር ቤት እየከፈሉት ያለዉን መስዋእትነት እጅግ በጣም እያደነቅን፣ በምንችለዉና አቅማችን በፈቀደ ሁሉ አገራችንን ኢትዮጵያ ለማዳን የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ እንደምንደግፍ፣ ከጎናቸዉም እንደምንሰለፍ ለማረጋገጥ እንወዳለን።

## አንድነት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር